

**ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስቶክሆልም**

**Debre Selam Kidist Mariam Etiopiska Ortodoxa Tewahedo Kyrka, Stockholm**

# የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን

# መተዳደሪያ ደንብ

## ዓላማ

1. በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ እምነትና ትውፊት መሠረት ሃይማኖታዊ ሥራዎችን ለማካሄድ የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ የቅድስት ማርያም ቤተ ክርስቲያን ተቋቁሟል።
2. ቤተ ክርስቲያኑ የአባሎቹን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ፍላጎቶች ለማሟላት የሚጥር ይሆናል።
3. ቤተ ክርስቲያኑ ነፃ የሆነና በራሱ የመተዳደር አቋም ይኖረዋል።

## መቀመጫ

የቤተ ክርስቲያኑ ሚደበኛ መቀመጫ ስቶክሆልም ይሆናል።

## አባሎች

1. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ አማኞች የቤተ ክርስቲያኑ አባሎች ለመሆን ይችላሉ።
2. ዕድሜአቸው አሥራ ስምንት ዓመትና ከዚያ በላይ የሆኑት አባሎች ዓመታዊ የአባልነት መዋጮ ይከፍላሉ።





3. የአባልነት መዋጮ የከፈሉ አባሎች ድምጽ የመስጠትና በቤተ ክርስቲያኑ ጠቃሚ ነገሮችና ሥራዎች የመካፈል መብት አላቸው።
4. የቤተ ክርስቲያኑን ዓላማና እምነት የሚጻረር አባል ከሥራ አስኪያጁ ወሳኔ በኋላ ወዲያወኑ ከቤተ ክርስቲያኑ ይወገዳል። ይህ የሚስወገድ ወሳኔ በጠቅላላ ጉባኤ መጽደቅ ይኖርበታል።

## ጠቅላላ ጉባኤ

1. የቤተ ክርስቲያኑ ጠቅላላ ጉባኤ ከፍተኛው ወሳኔ ሰጪ አካል ነው። ጠቅላላ ጉባኤ በመጋቢት ወር የሚደረግ ዓመታዊ ጉባኤ ወይም ሥራ አስኪያጁ አካል ተገቢ ሲመስለው የሚጠራው ሌላ ጠቅላላ ጉባኤ ነው። ሃያ አምስት በመቶ የሚሆኑ አባሎች ሲፈልጉም ሌላ ጠቅላላ ጉባኤ ይጠራል።
2. እያንዳንዱ አባል በጠቅላላ ጉባኤ ዘንድ አንድ ድምጽ ይኖረዋል።
3. የጠቅላላ ጉባኤ ወሳኔ በድምጽ ብልጫ ይሰጣል። መተዳደሪያ ደንቡን ለመለወጥ በጉባኤው በተገኙት አባሎች ሰባ አምስት በመቶ ድምጽ የተደገፈ ወሳኔ ያስፈልጋል።
4. ከጠቅላላ ጉባኤና ከሌላ ጠቅላላ ጉባኤ ቢያንስ ከሁለት ሳምንት አስቀድሞ ለአባሎች የጽሑፍ ጥሪ በፖስታ ይላክላቸዋል። በጥሪወም ጉባኤ የሚደረግበት ጉዳይ ይመለከታል።
5. በየዓመታዊው ጉባኤ የሚከተሉት ጉዳዮች ይወሰናሉ፦
   - ሀ) የሥራ አስኪያጅ አካል፣ የሂሳብ መርማሪዎችና የአስመራጭ ምርጫ፤
   - ለ) የየኮሚቴዎች አባሎች።
   - ሐ) የሥራ አስኪያጁ አካል የሥራ መግለጫ፤
   - መ) የሂሳብ መርማሪዎች መግለጫ፤
   - ሠ) የሥራ አስኪያጁ አካል ከተጠያቂነት ነፃ መሆን።
   - ሰ) የበጀትና የአባልነት መዋጮ ልክ መቁረጥ።
   - ረ) ሌላ ጉዳይ።



**ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስቶክሆልም**
**Debre Selam Kidist Mariam Etiopiska Ortodoxa Tewahedo Kyrka, Stockholm**

## የሥራ አስኪያጅ አካል

1. የቤተ ክርስቲያኑ የሥራ አስኪያጅ አካል ለአንድ ዓመት የሚመረጡ አምስት አባሎችና ሁለት ተለዋጮች ይኖሩታል።
2. የሥራ አስኪያጁ አካል ከጉዳዮች መሀል የሚከተሉትን ያደርጋል፦

   ሀ) ለቤተ ክርስቲያኑ ሥራ የሚያስፈልጉትን ዕቃዎች ማቅረብና በአገልግሎት ለማዋል እንዲችሉ ማድረግ።

   ለ) ቄስና ዲያቆን በሥራ ውል መቅጠር።

   ሐ) አስፈላጊ ኮሚቴዎችን ማቋቋም።

   መ) ሂሳብ መርማሪዎች የቤተ ክርስቲያኑን አስተዳደርና የሂሳብ ሁኔታ ለማየትና በአስተዳደሩ አካልም ሆነ በኮሚቴ ስብሰባ ለማግኘት እንዲችሉ ማድረግ።

   ሠ) በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ሃይማኖት ስር ካሉ ከሌሎች ቤተ ክርስቲያኖች ጋር ግንኙነትን ማበጀት።

## የመተዳደሪያ ደንብ ለውጥ

1. ይህ መተዳደሪያ ደንብ ለለወጥ ወይም በሥራ መዋሉ ሊቀር የሚችለው በሁለት ተከታታይ ጠቅላላ ጉባኤዎች፣ አንደኛቸው የዓመት ጉባኤ በሆነው፣ በሚተላለፉ ውሳኔዎች መሠረት ይሆናል።
2. ማኅበሩ እንዲፈርስ በሚደረግበት ጊዜ የሚገኘው ንብረት የቤተ ክርስቲያኑን መንፈስ የሚከተል የበጎ አድራጎት ዓላማ ላለው ማኅበር እንዲተላለፍ ይደረጋል።

ይህ መተዳደሪያ ደንብ በማኅበር ማቋቋሚያው ስብሰባ መጋቢት ፳፩ ቀን ፲፱፻፺፯ ዓ ም ጸደቀ። //(2005-03-30)//



# ደብረ ሰላም ቅድስት ማርያም የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋህዶ ቤተ ክርስቲያን ስቶክሆልም

**Debre Selam Kidist Mariam Etiopiska Ortodoxa Tewahedo Kyrka, Stockholm**